# የሶላር ፓኔሎችን በቤትዎ በነጻ መግጠም ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሃብት ይወቁ።

ነዋሪዎች በቤታቸው ሶላር ፓኔሎችን **ያለምንም ክፍያ** ማስገጠም ይችላሉ። እኛ—የዲሲ መንግስት—በአካባቢው ከሚገኘው የሶላር ገጣሚ ጋር በመሆን ለቤትዎ የሶላር ፓኔልን ንድፍ አውጥቶ ለመግጠም የሚያስፈልገውን ወጪ ይሸፍናል። የሶላር ፓኔል ሲስተሞች የእርስዎን የ **ኤሌክትሪክ ወጪ በአመት እስከ $500** ድረስ ይቀንሳሉ።

ይህ ፕሮግራም Solar for All እና Solar Works DC ይባላል። ይህ ፕሮግራም የቀረበው በኢነርጂ እና አካባቢ ዲፓርትመንት በአካባቢው ካለ ለትርፍ የማይሰራ ድርጅት ከሆነው ከ DC Sustainable Energy Utility (DCSEU) እና GRID Alternatives Mid-Atlantic ጋር በመተባበር ነው።

## ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

እነዚህ መግለጫዎች**በሙሉ** እውነት ከሆኑ፣ ብቁ ነዎት ማለት ነው:

- የሚኖሩት በተከራዩት ወይም የራስዎ በሆነ የአንድ ቤተሰብ ቤት ውስጥ ከሆነ (ወይም አራት ወይም አምስት ክፍሎች ያሉት ህንጻ)።
- ቤትዎ የሚገኘው ዲሲ ውስጥ ነው።
- የእርስዎ ስም ወይም በቤተሰብዎ ውስጥ ያለ የሆነ ሰው ስም ወይም አከራይዎ ፍጆታ ክፍያዎ ላይ ከተዘረዘረ።

- እንዲሁም ከእነዚህ መግለጫዎች ውስጥ **አንዱ** ትክክል ከሆነ:
    - ቤተሰብዎ ከእነዚህ ፕሮግራሞች ውስጥ ቢያንስ ከአንዱ[የፍጆታ እርዳታ] ወይም ድጋፍ ያገኛል፡ ተጨማሪ የምግብ ድጋፍ ፕሮግራም (SNAP)፣ ጊዜያዊ ድጋፍ እርዳታ ለሚፈልጉ ቤተሰቦች (TANF)፣ ተጨማሪ የደህንነት ገቢ (SSI)። ***ወይም***

- የቤተሰብዎ አመታዊ ጠቅላላ ገቢ— ታክስ ከመክፈልዎት በፊት ያለዉ ገቢ — በቤተሰብዎ መጠን መሰረት ከገደቦቹ በታች ወይም እኩል ነዉ። ገቢን ለማስላት፣ ከሚኖሩበቻዉ ወጣቶች ጋር ያለን በስራ የተገኘ ገንዘብ ታክስ ከመክፈልዎ በፊት ይደምሩ። ከዚያም፣ ከማህበራዊ ደህንነት፣ ከስራ አጥነት፣ ከልጅ ድጋፍ ወይም ከጡረታ ክፍያዎች የሚገኙትን አብረዎት ከሚኖሩት ማንኛዉንም ሰዎች የተገኘ ገንዘብ ይደምሩ። (ከ 18 አመት በታች የሆኑ ልጆችን ያጠቃልላል)። ከዚህ በታች ምልክት ያድርጉ።

| **የቤተሰብ መጠን** (ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውንም ሰው ይቁጠሩ) | **ከፍተኛው የቤተሰብ ገቢ** |
|---|---|
| 1 | $70,600 |
| 2 | $80,650 |
| 3 | $90,750 |
| 4 | $100,800 |
| 5 | $110,900 |
| 6 | $121,000 |
| 7 | $131,050 |
| 8 | $141,150 |
| 9 | $151,200 |
| 10 | $161,300 |

# ያመልክቱ።

የመጀመሪያውን ደረጃ በኦንላይን ወይም በስልክ መጀመር ይችላሉ፡

- [የኦንላይን የፍላጎት ቅጽን](#) ይሙሉ። የእርስዎን ብቁነት ለማረጋገጥ እና በአካባቢው ካለ የሚገጥም ሰው ጋር ለማገናኘት፣ DCSEU በ 2 የስራ ቀናት ውስጥ ይደውልልዎታል ወይም ኢሜይል ያደርግልዎታል። ብቁ ከሆኑ፣ በአካባቢው ያለ የሚገጥም ሰው ቤትዎን ለመጎብኘት መርሃ ግብር ያወጣል እንዲሁም ጣሪያዎን ይፈትሻል።

*ወይም*

- በአካባቢው ካሉ የሚገጥሙ ሰዎች (ከስር የተዘረዘሩት) አንዱን ይጥሩ እና ሶላር ለሁሉም ላይ ፍላጎት እንዳለዎት ያሳውቋቸው። ስለብቁነትዎ አንዳንድ ጥያቄዎችን ይጠይቁዎታል እና ቤትዎን ለመጎብኘት እና ጣሪያዎን ለመፈተሽ መርሃ ግብር ያወጣሉ።

    - Greenscape Environmental Services, Inc. at (202) 373-9803
    - GRID Alternatives Mid-Atlantic (Solar Works DC) at (202) 602-0191
    - Ipsun Solar at (866) 484-7786
    - Solar Solution LLC at (202) 249-1112
    - WDC Solar, Inc. at (202) 506-7586

በማንኛውም ጊዜ ማመልከት ይችላሉ።

# ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

# ካመለከትኩ በኋላ ምን ይፈጠራል?

1. የሚገጥመው ሰው ቤትዎን ከመጎብኘቱ በፊት ለእርስዎና ለቤተሰብዎ አባላት የሚከተሉትን ሰነዶች ይሰብስቡ።
    - ፎቶ ያለባቸው መታወቂያዎች (ልክ እንደ መንጃ ፈቃድ ያሉ)
    - የእርስዎ ስም፣ በቤተሰብዎ ውስጥ ያለ የአንድ ሰው ስም ወይም የአከራይዎ ያለበት ከ PEPCO የተሰጠ የቅርብ የኤሌክትሪክ ክፍያ ወይም የእርስዎን የኤሌክትሪክ ክፍያ ለመክፈል በቤትዎ ውስጥ ያለ አንድ ሰው ቤትዎ የእርሱ እንደሆነ ወይም ሃላፊነት እንዳለበት ማሳየት አለበት።

- የቅርብ የክፍያ ደረሰኞች፣ የማህበራዊ ዋስትና መግለጫዎች፣ የጡረታ መግለጫዎች፣ የስራ አጥ ጥቅማ ጥቅም መግለጫዎች፣ የልጅ ድጋፍ መግለጫዎች፣ እና/ወይም የታክስ ተመላሾች

2. ቤትዎን ተከራይተውት ከሆነ፣ የሶላር ፓኔሎቹን ለመግጠም አከራይዎን በጽሁፍ ፈቃድ (በኢሜይል ወይም በደብዳቤ) መጠየቅ ያስፈልግዎታል።
3. የቤትዎን ጣሪያ እና የኤሌክትሪክ ፓኔል ለመፈተሽ የሚገጥመው ሰው ቤትዎን ይጎበኛል። ጉብኝቱ ብዙ ጊዜ ከ 1-2 ሰዓታት ሲፈጅ በጉብኝቱ ጊዜ ቤት መሆን ይኖርብዎታል። የሚገጥመው ሰው በኮቪድ-19 ምክንያት ንክኪን ለመገደብ ሙከራዎችን ያደርጋል እና እርስዎና የሚገጥመው ሰው ተጨማሪ የደህንነት ጥንቃቄዎችን ማድረግ ይኖርባችኋል።

4. ጣሪያዎ የሶላር ፓኔሎቹን ክምደት መሸከም ከቻለ እና በቂ የሆነ የጸሓሀ ብርሃን ካገኘ፣ የሚገጥመው ሰው የማመልከቻ ቅጹን በእንግሊዝኛ ወይም ስፓኒሽ እንዲያጠናቅቁ በመርዳት በፕሮግራሙ ለመመዝገብ እና በደረጃ 1 ላይ ያሰበሰቧቸውን የሰነዶች ቅጂ ለመሰብሰብ ያስችላል።

5. የሚገጥመው ሰው ለሶላር ፓኔሎቹ ሲስተም አገጣጠም፣ ስምምነት እና ዋስትናዎች አብሮዎት ይሆናል።
6. ለሶላር ፓኔል ሲስተሙ መግጠሙን ከጨረሱ በኋላ፣ ገጣሚው ሰው ከዲሲ የሸማቾች እና የቁጥጥር ጉዳዮች መምሪያ (DCRA) ለፈቃድ ያመለክታል። እንዲሁም ከዲሲ የኤሌክትሪክ አቅራቢ ከሆነው Pepco የእርስዎን የመሳሪያ ገጠማ ፈቃድ ለመስጠት ማመልከቻ ያስገባሉ። የሚገጥመው ሰው ከ DRCA እና Pepco ፈቃድ ለመቀበል በመደበኛነት እስከ 4 ሳምንታትን ይፈጃል።

7. የሚገጥመው ሰው ከ DCRA እና Pepco ፈቃዶችን ሲያገኝ፣ የሶላር ፓኔል ገጠማውን ለማካሄድ ከእርስዎ ጋር መርሃ ግብር ይይዛሉ። በአየር ሁኔታው ላይ ተመስርቶ፣ ገጠማው ከ 2-4 ቀናትን መውሰድ ያስፈልገዋል።

8. DRCA እና Pepco የእርስዎን የሶላር ፓኔል ሲስተም፣ ከተገጠመ ከ 3-4 ሳምንታት ውስጥ ይፈትሻሉ።
9. የእርስዎን የሶላር ሃይል ምርት ለመከታተል Pepco የእርስዎን ቆጣሪ ይቀያይራል።
10. ለእርስዎ የሚገጥመው ሰው ሁሉም ነገር እየሰራ እንደሆነ ለማረጋገጥ፣ ከእርስዎ ጋር ክትትል ያደርጋል። በእርስዎ የሶላር ሲስተም ላይ ማንኛውም ችግር ቢከሰት፣ ለእርስዎ የሚገጥመው ሰው ለ 20 አመታት የጥገና እርዳታ ያደርጋል።

11. የ 20 አመት የውል ጊዜው ሲያበቃ፣ ሲስተሙን ከስራ ተቋራጩ ለመግዛት እርስዎ ብቁ ይሆናሉ።

ብቁ ከሆኑ ነገር ግን ጣሪያዎ የሶላር ፓኔሎቹን ክብደት መሸከም የማይችል ከሆነ ወይም በቂ የሆነ የፀሃይ ብርሃን የማያገኝ ከሆነ፣ ኤሌክትሪክዎን በአካባቢው ከሚገኘው የሶላር ሃይል አቅራቢ በማግኘት ወደ ሶላር አሁንም ቢሆን መቀየር ይችላሉ።

# ሁሉም ብቁ አመልካቾች የሶላር ፓኔል አስገጥመዋል?

አይ፣ ለሶላር ፓኔል ሲስተሞች የሚሰጠው ገንዘብ መጀመሪያ በመጣ፣ መጀመሪያ

በተስተናገደ መሰረት ላይ ያለ ነው።

# ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?

ቢያንስ በአመት አራቴ፣ በሲስተሙ ኢንቨርተር ላይ ያለውን ምስል በመፈተሽ የሶላር ፓኔል ሲስተምዎ እየሰራ መሆኑን ማረጋገጥ አለብዎት። የእርስዎ ገጣሚ ሰው ይህ እንዴት እንደሚደረግ ያስተምርዎታል።

# ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?

መጀመሪያ፣ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን በገጹ የታችኛዉ ስፍራ ላይ ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን ለሁሉም የስልክ መስመሮች የእኛን Solar for All የስልክ መስመር በ(202) 299-5271 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ ከ 9 am እስከ 5 pm ባለዉ ጊዜ ያግኙን። ወይም የ Solar for All ቡድንን በ solarforall@dc.gov ላይ በርእሰ መስመር “Single Family Solar for All Question” በማለት ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

እንዲሁም የእኛን አጋር DCSEU ከጥያቄዎችዎ ጋር በ (202) 479-2222 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ፣ ከ9 am እስከ 5 pm ድረስ ማነጋገር ይችላሉ ወይም “Single Family Solar for All Question” በሚል ርዕሰ መስመር በመጠቀም በ solar@dcseu.com ላይ ይላኩ።

## ቤቴን የበለጠ ለአካባቢ ተስማሚ ለማድረግ አሁንም ቢሆን እርዳታ ያስፈልገኛል። ምን ማድረግ አለብኝ?

በእኛ የአካባቢያዊ ሀብቶች ገጽ ላይ እርስዎን ሊረዱ ስለሚችሉ ሌላ መረጃዎች ማግኘት ይችላሉ። በፍጆታዎችዎ ላይ ገንዘብ ለመቆጠብ ስለሃብቶቹ የበለጠ ማወቅ ይችላሉ።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## ለዚህ ፕሮግራም ገቢዬ ከገደቦቹ በላይ ነው ነገር ግን የሶላር ፓኔሎቹን ለመግጠም አሁንም እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?

ነዋሪዎች ሶላር ላይ ያለገንዘብ ድጋፍ እንዴት መዋዕለ ንዋያቸውን ሊያፈስሱ እንደሚችሉ በእኛ ወደ ሶላር መሄድ የሃብት ገጽ ላይ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## የሶላር ፓኔሎቹን በቤቴ ከገጠምኩ በኋላ የኤሌክትሪክ ክፍያ አሁንም ይመጣብኛል?

አዎ። በቤትዎ ሶላር ፓኔሎችን መግጠም በዓመት ያለውን የኤሌክትሪክ ክፍያ በ $500 እንዲቀንስ በማድረግ ይረዳል ነገር ግን ከከተማው የኤሌክትሪክ ማሰራጫ የኤሌክትሪክ ሃይል ድርሻዎን ማግኘትዎን ይቀጥላሉ። የእርስዎ ወርሃዊ የኤሌክትሪክ ክፍያ በሶላር ፓኔልዎ ለመነጨው ሃይል ክሬዲትን የሚያጠቃልል ይሆናል።

## የሶላር ፓኔሎቹን ለመግጠም ቤቴ የራሴ መሆን ያስፈልገዋል?

አይ። የገቢ መስፈርቶቹን የሚያሟሉ ተከራዮች አከራዮቻቸው እስከተስማሙ ድረስ ለዚህ ፕሮግራም ብቁ ናቸው።

## የሶላር ሃይል የሚሰራው እንዴት ነው?

የጸሃይ ፓናሎች ከጸሃይ ሃይል ይስቡና እርስዎ ሊጠቀሙበት ወደሚችል ኤሌክትሪክ ይለውጡታል። ኤሌክትሪኩ ከዛ ወደ ቤትዎ በመተላለፍ ለኤሌክትሪክ መሳሪያዎች ሐይል

ይሰጣል። ከእርስዎ ሶላር ፓኔሎች የሚመጣ ያልተጠቀሙበት ማንኛውም የኤሌክትሪክ ሃይል ሌሎች ሰዎች እንዲጠቀሙበት ወደ ዋናው የኤሌክትሪክ ማሰራጫ ይላካል።

## በእኔ የሶላር ፓኔሎች ለሚመነጨው ሃይል ገንዘብ ማግኘት እችላለሁ?

የቤት ባለቤቶች በሶላር ፓኔላቸው ለመነጨው ሃይል ከፍጆታ ድርጅቶች ብር ሊያገኙ ይችላሉ። እኛ—የዲሲ መንግስት— የፍጆታ ድርጅቶችን እንደ ፀሃይ ካሉ ታዳሽ ሃይሎች የኤሌክትሪክ የተወሰነ መቶኛ ድርሻቸውን እንዲያመነጩ እንጠይቃለን። እነሱ ያንን መስፈርት የማያሟሉ ከሆነ፣ ቅጣት ይከፍላሉ አልያም የሶላር ታዳሽ ሃይል ሰርተፍኬቶች (ወይም SRECs) ከሶላር ፓኔል ባለቤቶች ይገዛሉ። ስለ SRECs የሶላር ገጣሚዎን ይጠይቁ እና ከ SREC ደላላ ጋር እንዲገናኙ ይረዱዎታል። የሚያገኙት መጠን በገበያው ዋጋ እና ከፍጆታ ድርጅቶቹ ጋር ባለው ስምምነቶች ላይ የተመሰረተ ነው። ከ Environmental Protection Agency (የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ) ስለ SRECs የበለጠ ይወቁ።

## የሶላር ፓኔሎቹ ጥገና ይፈልጋሉ?

ሶላር ፓኔሎቹ ቶሎ ቶሎ ጥገና አይፈልጉም ነገር ግን በትክክል እየሰሩ እንደሆነ ለማረጋገጥ ሲስተሙን ለጥቂት ጊዜ መፈተሽ ጥሩ ነገር ነው። የእርስዎ ስራ ተቋራጭ ወይም ሶስተኛ ወገን ኦፐሬተር የሶላር ሲስተምዎን እስከ 20 አመታት ድረስ እንዲጠብቁ ያግዝዎታል።

## ፓኔሎቹን በቤቴ መግጠም ባልችልም ወደ ሶላር መቀየር እችላለሁ?

አዎ። ጣሪያዎ የሶላር ፓኔሎቹን ክብደት መሸከም ካልቻለ ወይም በቂ ፀሃይ ማግኘት ካልቻለ፣ በአካባቢው ካለ የሶላር ሃይል አቅራቢ ኤሌክትሪክ በማግኘት አሁንም ወደ ሶላር መቀየር ይችላሉ።

## የፍጆታ ክፍያዎቼን የምቆጥብባቸው ሌላ መንገዶች አሉ?

አዎ። ለእርስዎ የሚገጥመው ሰው ለ ኤሌክትሪክ፣ ጋዝ፣ ዘይት እና/ወይም የውሃ ክፍያዎ እርዳታ ለማግኘት እንዲመዘገቡ ግብዣ ያቀርብልዎታል። በፍጆታዎችዎ ላይ ገንዘብ ለመቆጠብ ስለሃብቶቹ የበለጠ ማወቅ ይችላሉ።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።*